# ከፍለን እናታግል
# <u>ከቀለሉ አይቀር እንደ ገለባ . . .</u>

**<u>ከበልጅግ አሊ</u>**

**- ፩ -**

የሜክሲኮ ታዋቂ ደራሲ የሆነው ማሪዮ ቤላቲን (Mario Bellatin) በቅርብ ቀን በሄራልድ ትሪቡን ላይ አንድ ጽሁፍ አስነብቦኝ ከልቤ አሳቀኝ ። ማሪዮ በሜክሲኮ ሃገር አንድ በጣም የሚገርም የኪራይ ጥበብ በመባል የሚታወቅ ልምድ መኖሩን በመግለጽ ነበር የጻፈው። ለምሳሌ መጠጥ ጠጥተው መኪና ሲነዱ ከተገኙና ሁለት ቀን እስር ከተፈረደብዎት ላይታሰሩ ይችላሉ ። ለሌላ ሰው ከፍለው በእኔ ስም እሱ ይታሠርልኝ ብለው በእርስዎ ፈንታ እንዲታሰርልዎት ማመልከት ይችላሉ ። ፖሊስም ሰውየውን አስሮ እርስዎን ይለቅዎታል ።ዘመድ ከታመመብዎትና፣ በሐኪም ቤቱ ሕግ ዘመድ አብሮ ማደር ካለበት፣ እርስዎም ጊዜ ከሌለዎት በሐኪም ቤቱ አካባቢ በዚህ ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች አይታጡም ። እናት ወይም ሚስት ወይም የቅርብ ዘመድ ነኝ ብሎ በእርስዎ ስም የሚያድር ፈልገው ተከራይተው ማሳደር የተለመደ ነው ። ጠላትዎን ማስደብደብ ከፈለጉም ጉልበተኛ በመቅጠር ማስቀጥቀጥ ቀላል ነው ። ለማስገደልም እንደዚሁ ። ማሪዮ ስላቁን በመቀጠልም መጻፍ ሰልችቶኛልና በእኔ ስም ጽፎ መጽሐፍ የሚያወጣልኝ እፈልጋለሁ ብሎ በቀልድ መልክ አስቀምጦታል።

ዛሬ በዓለም ላይ ያሉ መሪዎች በሕዝብ ፊት የሚያቀርቡትን ንግግር በሌሎች ጸሀፊዎች እንደሚያጽፉ የታወቀ ነው ። መጽሐፍም በስማቸው ያሳተሙ ትንሽ አይደሉም ። የሚገርመው ግን እነዚህ ስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች በሌላ ሰው አጽፈው የሚያስነብቡትን እራሳቸው እንደጻፉት ተደርጎ ንግግር አዋቂ ፣ የተማሩ ፣ የተመራመሩ ናቸው ተብለው ሲሞገሱበት ይሰማል ። ለመለስ ሌሎች ሰዎች ጽፈው እንደሚያቀርቡለት የታወቀ ቢሆንም ወያኔን አፍቃሪ የሆኑ ግለሰቦች ስለ መለስ ንግግር አዋቂነት በአድናቆት ሲናገሩ ሰምታችሁ ይሆናል ።

በተለያዩ ሥርዓቶች ውስጥ መንግሥትን ደግፈው፣ መንግሥት የሚፈልገውን የሚጽፉ፣ እንዳሉ ሁሉ መንግሥትን ተቃውመው፣ መከራ የደረሰባቸው ፣ ሕይወታቸውን ያጡ ብዙ ናቸው።(በዓሉ ግርማ፣ አቤ ጉበኛ . . . በዋቢነት ይጠቀሳሉ። ) የዚያኑ ያህልም መንግሥትን ደግፈው ሌሎች ደራሲያንን ያስገደሉ፣ ያሰቃዩ፣ ያሳሰሩ ጸሐፊዎች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። እነዚህን ከመሳሰሉቱ በተራቸው ጊዜ ተለውጦባቸው በስደት ላይ የሚገኙት በርካታ ናቸዉ ።

ደራሲያንን ሕብረተሰቡ በአመኔታ የሚቀበላቸው ሕዝባዊ አመለካከት ካላቸው ብቻ ነው። አንድ ሕዝባዊነት ያለው ደራሲ ለእኩልነት ፣ ለአንድነት ፣ ለነፃነት በሚያደርገው ትግል መከራ፣ ስቃይ፣ እስርና ፣ እንግልት ሊያስከትልበት እንደሚችል ማመንና መቀበል አይገደዉም።ስደት ፣ እስር ፣ ግርፋትና ስም ማጥፋት ጨቋኝ መንግሥታት እውነተኛ በሆኑ ደራሲያን ላይ ሞራላቸውን ፣ እምነታቸውንና ትግላቸውን ለመስበር ከሚጠቀሙባቸዉ መንገዶች ጥቂቶቹ ናቸዉ ።

ሥልጣን ላይ ያሉ ጨካኝና ጨቋኝ መንግሥታት ደራሲያንን እያስገደዱ ፣ እያስፈራሩ ሥልጣናቸው ላይ ለመደላደል እያሞገሱ፣ እያሞካሹ እንዲጽፉላቸው ያዛሉ ፡ ያባብላሉም። የመንግሥታቸውንም ዓላማ እንዲያስፋፉላቸው ያስገድዳሉ ፡ ይደልላሉም። እንቢ ከተባሉ ደግሞ እስከመግደል ደረጃ ይደርሳሉ ።እነዚህን ጨቋኝ መንግሥታት መንግሥታቸውን የሚቃወሙ ድርሰቶች ለሕዝብ እንዳይደርሱ የሳንሱር መቀስ አዘጋጅተው ይከላከላሉ ።

በአሁኑ ጊዜ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ይህንን የሳንሱር መቀስ እየተፈታተነው ይገኛል ። የሕዋ ግንኙነት (Internet) ከሁሉም በበለጠ በሕዝብ ዘንድ ተጠቃሚነት አግኝቷል። ሕዝብ እውነትን ለማወቅ ጥረት ስለሚያደርግ በየድረ ገጹ የተጻፉትን መከታተሉ አይቀሬ ነው ። ብዙ መንግሥታት ይህንን ለማቆም የሚቃወሟቸውን ድረ ገጾች ለሕዝብ እንዳይደርሱ ይከለክላሉ ። ።በኢትዮጰያ፣ በኢራን ፣ በቻይና ፣ በኩባ እንዲሁም በበሌሎች ሃገሮች ይህ ችግር በጉልህ ይታያል።ለምሳሌ በሃገራችን እንዳይታዩ በወያኔ የታገዱ ድረ ገጾች ብዙ ናቸው። ወያኔ ድረ ገጾቹ እንዳይታዩ በመከልከል ብቻ ሳይታቀብ ቴክኖሎጂው ሃገር ውስጥ እንዳይስፋፋም አንቆ ይዞ ይገኛል ።

ወያኔ በሃገር ውስጥ ያሉትን ነፃ ሜዲያዎች እየዘጋ ፣ ጋዜጠኞቹን እያሰረ ፣ ደራሲዎችን እየገረፈ ፣ እየገደለ፣ እያሳደደ የሕዝብን የማወቅ መብት ገፎ የራሱን ደጋፊዎች ብቻ ነፃ አድርጎ በባዶ ፕሮፖጋንዳቸው ሕዝቡን ያሰለቹታል ። በዚህም ምክንያት ደግሞ በውጭ አገር ሕዝቡ ስለሀገሩ ሁኔታ እንዲያውቅ ፣ እንዲወያይ በሚፈልጉ ወገኖች የተለያዩ ድረ ገጾች ፣ ራዲዮኖች፣ ጋዜጣዎች ተከፍተው አገልግሎታቸዉን በመስጠት ላይ ይገኛሉ ።

የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን በስደት ከተቋቋሙት ሜዲያዎችም መሀከል ጥቂቶቹ ራሳቸዉ በራሳቸዉ ላይ የሳንሱር ማዕቀብ የሚያደርጉ መሆኑ ነዉ ።ድረ ገጾቹ ባለቤቶቻቸው የማይደግፉትን አቋም የያዘ ጽሁፍ በፍፁም እንዳይወጣ ይከለክላሉ ። ባለፈው ወር "የተደበቀው ድርቅ " በሚል የጻፍኩትን መጣጥፍ አንድ የድረ ገጽ ባለቤት ያለፈ ታሪክ ነውና አላወጣም ብሎ ፃፈልኝ ። ከድርቁ ጋር ተያይዞ የመጣው ችግር  አልፏል -- አላለፈም የሚለውን የመከራከሪያ ምክንያት በማቅረብ የድረ ገጹ ገዥ የራሱን ውሳኔ በመወሰን የሌሎችን  የማንበብና የመተቸት መብት አግቶ አቁሞታል ። ምንም እንኳ ጽሁፉ በዚህኛው ድረ ገጽ ባለቤት ቢታገድም ሌሎች በዚህ ዓይነት ያልተመለከቱት ለንባብ አብቅተውታል ። በወቅቱ  ስለ ድርቁ እንድጽፍ ያስገደደኝ ጉዳይ ቢኖር በቅርብ ጊዜ ሰለ ወያኔና ድርቁ በውስጥ አዋቂዎቹ ቢቢሲ ላይ የተጋለጠው ዜና ነው ። ወያኔ በእርዳታው ገንዘብ መሣሪያ ይገዛበት እንደነበር በሰማሁ ጊዜ ፤በዛ ወቅት እኔ የማውቀውን በደርግ በኩል ሲደረግ የነበረውን አጣቅሼ ነበር ለሕዝብ ለማሳወቅ የጣርኩት። የዚህ ድረ ገጽ ገዢ እሱ የሚፈልገውን ብቻ እንድጽፍለት ነው የጠየቀኝ ። ካልሆነ ግን እንደምንለያይ አሳስቦኛል።  እንግዲህ ግለሰቡ ድረ ገጹን ለመጠቀም ከፈለግሁ እሱ የሚፈልገውን መጻፍ ሊኖርብኝ ነዉ ማለት ነዉ።እንግዲህ የድረ ገጾችን ባለቤቶች ለማስደሰትና ጽሁፋችን ለሕዝብ እንዲቀርብ ከፈለግን  ሳንወድ  ቅጥረኛ ጸሐፊ ልንሆን ነው ማለት ነው ። ይህ በጣም ያሳዝናል ። ዘለፋ ፤ስድብ ፤ አጥንት ሰባሪ ፤ ትዳር ከልካይ የሆነ ጽሁፍ በሆነና ቢከለከል ምንም ባልነበር ። ታሪክን ወደ ኋላ አመላክቶ ለሕዝብ የተጻፈን መከልከል  ከጀመርን ከሀገር ካሳደዱንና ከምንዋጋቸው ጉልበተኛ ገዥዎች በምን ልንሻል ነው?

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ በሃገር ውስጥ ያለውን ነፃ ፕሬስ በመዝጋቱ በውጭ ሃገር በአሁኑ ወቅት ብዙ መጽሐፍት እየተጻፉ ነው ። በተለይ በመንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የነበሩ ግለሰቦች፣ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት የሚያውቁትን ምስጢር እያወጡ  ይጽፋሉ ። የደራሲያኑ ዓላማ የተለያየ ነው። ለሕዝብ እውነትን ለማድረስ ከሚጥሩት ባሻገር ፤አንዳንዶቹ ለንግድ ፤ ሌላቹ ደግሞ ከሠሩት  ወንጀል ነፃ ነን ብለው ለመከላከል ወይም አሁን ጠላቴ ነው ብለዉ የሚያስቡትን ግለሰብ ስም ለማጥፋት ፤ ለመወንጀል ሊሆን ይችላል።። ይህንን ተንኮል ሕዝቡ በሁሉም ወገን የተጻፈውን አንብቦ ፍርድ እንዲሰጥ ድረ ገጾች ትችቶችን በማውጣት ሊተባበሩ ይገባል ።

ግን እውነቱን ለማወቅ በሚደረገው ጥረት ድረ ገጾች ታላቅ አስተዋፅዖ ቢኖራቸውም  በደራሲዎቹ ደጋፊና ተቃዋሚ ተከፋፍለው ፍልሚያ ውስጥ በመግባት አንድ ወገናዊ የሆነውን አመለካከት ብቻ ሲያራምዱ ይታያሉ ። ይህ ደግሞ  ወገናዊ የሆነን አመለካከት ያስፋፋል እንጂ ወደ እውነቱ አያስጠጋንም።  የድጋፍ ትችትን ያሰፈረ ድረ ገጽ የተቃውሞን ቢያስከትል አንባቢዎቹን ሙሉ የሆነ አመለካከት እንዲኖራቸውና የራሳቸው የሆነውን አቋም እንዲይዙ ይረዳል ። ግን የሚያሳዝነው ድረ ገጾቹ ከፖለቲካ አቋማቸው አንፃር ደራሲውን ስለሚመለከቱ  ወገንተኛነትን አብዛኛዎቹ ያሳያሉ ።

በአሁኑ ወቅት የተጻፉትን ከተመለከትን የተስፋዬ ገብረ አብን መጽሐፍን የሚያክል ብዙ የተነገረለት፣ የተጨበጨበለት፣ የተደገፈ ፤ የተተቸ፣ አለ ብዬ አለምንም ። የጋዜጠኛው ማስታወሻ የሚለውን ያነበብኩት ሲሆን "የደራሲው ማስታወሻ"ን ለማንበብ ጥረት አላደረግኩም ። በግል አቋሜ በሥልጣን ላይ ሆነው ሕዝብን ሲበድሉ ፤ ሲያንገላቱ የነበሩ ግለሰቦች ታሪካቸውን ጽፈው ለሽያጭ ካቀረቡት ላለመግዛት ወስኛለሁ ። ምን አልባት ግለሰቦቹ ገቢውን ለሕዝባዊ ተቋማት ገቢ እንዲውል ካደረጉ ብቻ ነው የምገዛው ።

መጽሐፉን  ስላላነበብኩ ለመተቸት አልችልም ። ግን ደራሲውን በጣም " አደንቃቸዋለሁ" ። "አደንቃቸዋለሁ"ስል መጽሐፋቸውን ሳታነብ እንዴት? ልትሉኝ ትችላላችሁ ። አዎ የማደንቃቸው በአካባቢዬ የተመለከትኩትን  በማገናዘብ ነው ። በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ መጽሐፍ አንባቢ ነው ብላችሁ የምታምኑ ካላችሁ ተላላዎች ናችሁ ። ብዙዎቻችን ቤታችን ከስልክ ማውጫ ያለፈ መጽሐፍ የለንም ። ምን አልባት  የባንክ ደብተር ይጨመር ይሆናል ። አሁን  ግን እንደታዘብኩት  ማንበብን በማያዘውትሩ ግለሰቦች እጅ ሳይቀር የተስፋዬ ገብረ አብን  መጽሐፍ ስመለከት ገርሞኛል። እንዲያው ጥሩ መጽሐፍ ጠፍቶ ነው ወይ  እነዚህ ሰዎች እስከ ዛሬ የማያነቡት  ? ብዬ ራሴን እንድጠይቅ ገፋፍቶኛል ። ሁኔታውንና ምክንያቱን ባውቀውም እኝህን ደራሲ ወይም ሰለመጽሐፉ የቀሰቀሰላቸውን ክፍል አድንቄአለሁ። ይህንን ማንበብ ያልለመደ ባተሌ ሁሉ ቢያንስ ቢያንስ  ባያነበው እንኳ መጽሐፉን ገዝቶ ከስልክ ማውጫው ጎን እንዲስቀምጠው፣ ጌጥ እንዲያደርገው፣ ውይይት በተነሳ ቁጥር እንዳንባቢ ራሱን እንዲቆጥር አድርገውታልና አደንቃቸዋለሁ ፡- ወንድ የአራዳ ልጅ ።

ጎረቤቴን ለብዙዎቻችሁ በተከታተይ ጽሁፍ  አስተዋውቄችሁ ነበር ።  የዘመኑ  ኢንቬስተሮቹ   ምርጫ ሲደርስ የሕዝቡ ቁጣ ሊያመጣ የሚችለውን ዱላ  በመፍራት ምርጫው እስከሚያልፍ ሃገሪቱን ጥለው እንደሚወጡት ጎረቤቴም  እኔ ወደ አለሁበት ሀገር በቅርብ ቀን ተመልሷል። ቤቱ ከመግባቱ  እየሮጠ ወደ ቤቴ መጥቶ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፡ -

- "የተስፋዬ መጽሐፍ አለህ ?"
- "የለኝም ።"
- "እንዴት ?"
- "አልገዛሁማ ።"
- "ሰው ሁሉ የተጋደለበትን ?"
- "ቢሆንም አልገዛሁም ። ለመሆኑ አንተ እንዴት ሰማህ አዲስ አበባ ይሸጣል እንዴ ?"
- "ከሰው ነው የሰማሁት ። ኤርትራዊ ነው አሉ ። የሻቢያ ቅጥረኛ ። ከዚህ በፊት አማራና ኦሮሞን ለማዋጋት ጥረት ያደረገ ። ነፃ ፕሬሱን ሲያንሳቁል የነበረ ። ጋዜጠኞች ወያኔን ደግፈው እንዲፅፉ የሚያስገድድ . . . . . ." በጥቂት ሰከንዶች ከማውቀውና ከሰማሁት በላይ የደራሲውን ስም አጎሳቆለው ። ይህንን ሁሉ ውንጀላ ስሰማ (ጎረቤቴ ለወያኔ ያደረበትን ፍቅር ተገንዝቤዋለሁና) ምን አልባት ወያኔን ያናደደ ዜና ይኖረው ይሆን ይሆን? በማለት ስለ ባለሥልጣናት መጽሐፍ በግሌ ራሴ ላይ የጣልኩትን ማዕቀብ ለማንሳት ዳድቶኝ ነበር ።

- "ታዲያ ድሮ ይህ ሰው እንዲህ ከነበር ለምን መንግስት ስልጣን ላይ አስቀመጡት? ለምንስ ቀድመው አላጋለጡትም?--- ድሮ ለእነርሱ ስለሚጽፍና ስለሚያሞግሳቸው ነው ? " ብዬ ጠየቁት።

- ጎረቤቴ ጥያቄን ትቶ በተቻለው መጠን ደራሲውን በመጽሐፉ ሳይሆን በፖለቲካ አቋሙ ከአጣጣለ በኋላ "አሁን እኮ ለኢሳያስ ነው የሚሰራው ። ከፈለግክ አሁን መጽሐፉን ልገዛ መሄዴ ነው ። ና እንሂድና እንግዛው " አለኝ

- ለጎረቤቴ አቋሜን ግልፅ አደረግኩለት ። የሠሩትን ግፍ ጽፈው ለሚሸጡና ዳግም በእኛው ትከሻ ላይ ሃብታም መሆን ለሚፈልጉ ገንዘቤን አውጥቼ ለሠሩት ግፍ ሽልማት አላደርግም አልኩት ። ጎረቤቴ አቋሜን ሲያውቅ ይሉኝታ ይዞት ቁጭ ብሎ ጨዋታውን ቀጠለ ።ጨዋታው ሲደምቅ መጽሐፉን መተቸት በሰፊው ተያያዘው። እንዳላነበበው ነግሮኛል። የሚተቸው ግን ካነበበው ሰው ባላይ ነው።ይህ የሚሆነው በሰማው ብቻ ነው ። ጎረቤቴን እስከማውቀው ድረስ ይቅርና አንድ መጽሐፍ አንድ ጋዜጣ ላይ የወጣ አነስተኛ ጽሁፍ የማንበብ ትዕግስት ያለው አይደለም። ብዙዎቹ የተስፋዬ መጽሐፍ ተቺዎች አንብበውት ላይሆን ይችላል። በየቦታው ግን አስሩን ሲያወሩ የምንሰማው ትችታቸው ወይም ድጋፋቸው በአንድ አካባቢ ነው ።

ተስፋዬን ከማይወዷቸው ፡ -

- ጥሩ የሥነ ጽሁፍ ችሎታ አለው ። ( የሚወዱትም የማይወዱትም ፣ የሚያነቡም፣ የማያነቡም እንደዚህ ብለው መጀመርን ይወዳሉ ።በዚህ ላይ የጋራ ስምምነት አለ ።
- አቋሙ ያጠራጥረኛል ።
- ኤርትራዊ ነው አንመነው ።
- በሞላ የሚያውቀውን ምስጢር አልነገረንም።
- የኢሳያስ ተላላኪ ነው ።
- በመለስ ላይ እኮ ብዙም አልጻፈም።

ተሰፋዬን ከሚወዷቸው ደግሞ ፡ -

- ጥሩ የሥነ ፅሁፍ ችሎታ አለው ።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ከተፃፉት መፃሕፍቶች መካከል ይህንን ያህል የተዋጣለት የለም ።
- ወያኔዎችን እኮ ጉድ አደረጋቸው ።
- ከፖለቲካ ድርጅቶች እሱ ይሻላል ።
- እነ ስዬን አጋለጣቸው ።
- እነ እከሌ እኮ ከእሱ ጋር ስለተጣሉ ነው ።
- ለወያኔም ሲሰራ እነስዬን አይወዳቸውም ነበር ።

ተስፋዬን ከሚተቹ ሰዎች የምንሰማው ባብዛኛዉ ይህን መሳይ ዝባዝንኬ የተሞላበት ነዉ ። በሥነ ጽሁፍ ችሎታው ላይ ሁሉም ምንም ችግር የላቸውም ። በፖለቲካ አቋሙ ላይ ግን በጣም የሠፋ ልዩነት ይታያል ። የተስፋዬ መጽሐፍ አንባቢዎችም ሆነ ተቺዎች ሌሎች መጽሐፍትን አንብበው ሲተቹ ወይም ሲያደንቁ ሰምተን አናውቅ ይሆናል ፡፡ በተለይ አንዳንዶቹ አዋቂ ለመባል የሚያደርጉት ጥረት መጽሐፉን አንድና ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈ አስመስለው ያቀርቡታል።ይህንን ለተመለከተው የተቺዎቹን ማይምነታቸውን አጉልቶ ነው የሚያሳየው ።

ግን ምንድነው አሁን ብዙዎችን መጽሐፉን ሊያስወድዳቸው የቻለው ? ብለን መጠየቃችን አይቀሬ ነው ።ተስፋዬ መጽሐፉን ከመጻፉቸው በፊት በብዙ ሰዎች ታላላቅ መጽሐፍትን ተጽፈዋል ፣ ታላላቅ ገጣሚዎች ተፈጥረዋል ፣ የፖለቲካ ትንታኔም ያቀረቡ ወገኖችም ብዙ ብለዋል ፣ ወያኔን ተስፋዬ ካጋለጠው በላይ እርቃኑን ያስቀሩትም ነበሩ ፣በአማርኛው ጥራትም የታወቁ መጽሐፍት ለንባብ በቅተዋል። እውነትንም በማግለጥ ረገድ ብዙ መጽሐፍት ተጽፈዋል ።ግን እንደ ተስፋዬ አልተደነቀላቸውም ።

የተስፋዬ መጽሐፍ ግን ሊደነቅ የቻለበት ምክንያት ለእኔ አንድ ነው ፡፡ ያም ተስፋዬ መጽሐፉ ውስጥ በየሰፈሩ የሚታማውን አቀነባብው በሚጣፍጥ ቋንቋ መጻፉቸው ነው ። ብዙዎቻችን በራሳችን ላይ የደረሰብንን መከራ ፣ መከራውን ካደረሱት ሰዎች ስንሰማው ይጣፍጠናል። በብዛት ልንሰማው እንፈልጋለን ። እንቅልፍ ይነሳናል ። የራሳችንን ጉዳት እናውቀዋለን ። ጎጂዎቻችን በዚያ ሰዓት ምን እንደሚያስቡ ለማወቅ እንጓጓለን ።መንግሥቱ መጽሐፍ ሊጽፍ ነው ብለን እንቅልፍ ነስቶን የምንጠብቅ ስንትቶቻችን ነን ? የሌሎቹንስ የወያኔ አባላት ? የደርግ የስለላ ሰራተኛ የነበረው የተስፋዬ ርስቴስ መጽሐፍ? ከሥነ ጽሁፉ ጥራት ጋር ሳይሆን ከቀድሞ ጌቶቻችን የደረሱብንን መከራ ከራሳቸው መስማት በመፈለግ ነው ። በዚህ ላትስማሙበት ትችላላችሁ ግን ሃቁ ይህ ነው ። ለገሰ አስፋው፣አሊ ሙሳ ፣መላኩ ተፈራ ወይም ሌሎቹም እንኳ ቢጽፉት መሰለፋችን አይቀርም ።

የደራሲው የሥነ ጽሁፍ ችሎታ ነው የሚሉትን አልስማማም። ምክንያቱም በቁም ነገር ብዛትም ይሁን በአማርኛው ጥራት ከጌታቸው ኃይሌ "አንድ አፍታ ላውጋችሁ" ሊወዳደር አይችልም ። አንዳፍታ ላውጋችሁ ሲደነቅም ሰምቼ አላውቅም።ፕሮፌሰር ጌታቸው በውጭ ያለው ሰው ምን ያህል አንባቢ እንደሆነ የማያቁት ይመስል ይህንን መጽሐፍ ግን አድንቀው ገዝተን እንድናነበው መምከራቸው ገርሞኛል ። ፕሮፌሰር ራሳቸው የደርግ ወይም የወያኔ አባል ቢሆኑና የሰው ነፍስ በእጃቸው ላይ ቢኖር ኖሮ ብዙ አንባቢን ያገኙ ነበር ።የማከብራቸው ፕሮፌሰር ጌታቸው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መጽሐፍ ቢጽፍ አንብቡት ጠቃሚ ነው፣ ውስጡ ቁም ነገር አለው እንደማይሉን አምናለሁ።ከመንግሥቱ እጅ ሽልማት አልቀበልም ያሉት ፕሮፌሰር ጌታቸው በመንግሥቱ የተጻፈን መጽሐፍ ለማምበብ ፍላጎት ይኖራቸዋል ብዬ አላምንም። አገሩን ለወያኔ ጥሎ ከበረረ ፋሽሽት አዲስ ነገር ይነግረኛል ብለው የሚጠብቁ አይመስለኝም ። የመርሴ ሃዘን ወልደ ቂርቆስ በቤተሰቦቻቸው የታተመው መጽሐፍ ብዙ ቁም ነገርም የሥነ ፅሁፍም ጥራት አለው ። ይህ መጽሐፍ መውጣቱን የሚያውቁ ስንቶች እንደሆኑ አላውቅም ። የበድሉ ዋቅጅራ ጥራት ያለው የግጥም መድበል አልተጨበጨበለትም ። ብዙዎቻችን ይህንን ጸሐፊ ማወቃችንን እንኳዋ እንጃ ።በእውቀቱ ስዩምን የምናውቅ ስንቶቻችንን ነን ? እነዚህን ልጥቀስ እንጂ ብዙ ጸሐፊዎች ተደብቀው ባሉበት ሃገር በስልጣን ላይ ሆነው ሲጨቁኑን ለነበሩ ሰዎች ወገባችንን እንሰብቃለን ።ስንቶች ያላነበብነውን ስናደንቅ ፣ ስንተች እንገኛለን? ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ "እስከ አሁን ከወጡት መጽሐፍቶች ሁሉ "ተብሎ ውድድር ሲገባ ነው ። ለመሆኑ ውድድሩ በምን በምን መስፈርት ነዉ የሚከናወነዉ ?

ብዙዎቻችን ወሬ እንወድዳለን ፣ አሉባልታ ይስበናል ፣ ስለ አሉባልተኞች ማወቅ ከፈለጋችሁ አንድ ጊዜ ስድብና አሉባልታ ወደሚበዛበት የፓልቶክ ክፍል ጎራ በሉ ። ክፍሉ ሰው በሰው ተጨናንቆ ታገኙታላችሁ ። ቁም ነገር የሚበዛበት ቦታ ደግሞ ብዙ ሕዝብ አታገኙም ። በመጽሐፉም ላይ የታየው ይኸው ነው ።የብዙዎቻችንን ቆሌ የሳበው በየመንደሩ በብዛት ሲታሙ የነበሩትን አሰባስቦ በተቀነባበረ መልክ መቅረቡ ነው ። ለምን ቀረበ የሚል አመለካከት የለኝም ። መጻፉ ጥሩ ነው ። ከአንባቢያንና ከተቺዎች ግን በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተጻፈ ተደርጎ የሚወሰደውን አልስማማም ። ሥልጣን ላይ የነበሩ ሰዎች ከስልጣን በተለያየ ምክንያት ሲወርዱ ታሪክን ሲያድበሰብሱና ራሳቸውን ለመከላከል ብለው እውነትን ሲያጥፉ ስንመለከት ዝም ማለት የለብንም ። እውነት በእውነተኝነቱ ሊፃፍ ይገባዋል እንጂ ሊቀነስ፣ ሊጨመር፣ ሊቆረጥ ፣ሊቀጠል ፣ሊጣመም . . . አይገባም ።በተለይ ወያኔን በሚመለከት ብዙ መረጃ የሚስፈልገን አይመስለኝም ። ለመሆኑ ወያኔ ሃገራችንንና አንድነታችንን በአደባባይ ሲፈታተን ላለፉት አስራ ስምንት ዓመታት በይፋ ከመመልከት በላይ ምን መረጃ ያሻል ????

ምን አልባት የተስፋዬ መጽሐፍ እዩኝታዉ ወቅታዊነቱ ነው ልትሉኝ ትችላላችሁ ። አይደለም ። ሌሎች ወቅታዊ የሆኑ መጽሐፍትም እንደዚህ አልተረገደላቸውም ። የሌላው አሉባልተኛ የተስፋዬ ርስቴም መጻሐፍ አንድ ሰሞን ስንታመስበት ነበር ። ተስፋዬ ርስቴ የወገኖቻችን ደም በእጁ ላይ ያለበት፣ የደርግ ፅሕፈት ቤት መርማሪ የነበረ ሻምበል ነው ። የጻፈው የአሉባልታ ስብስብ ዓላማ እኔ ንፁህ ነኝ በሚል መከለያ፣ ወንጀሉን መሸፋፈን ነው ። ውሸትና አሉባልታን መጻፍ አንድ ደራሲን ሊያስወቅሰው እንጂ ሊያስከብረው ብሎም በሸያጩ እንዲከብርበት ሊፈቀድለት አይገባም ፡፡ በዚህ አያያዛችን መለስ ነገ ተራዉ ደርሶ ከሃገር ሲወጣ ስለመጦሪያዉ ማሰብ ላይኖርበት ነዉ ፡፡ ምነዉ ቢሉ በዉሸትና በቀደዳ የሚስተካከለዉ የታጣለቱ መሰሪ ሰዉ እጽፍ ማለቱ አይቀሬ የመሆኑን ያህል ላንብብ ባዩም በወረፋ ሰልፍ ማጨናነቁን ከወዲሁ መገመት አዳጋች አይደለም።

አንዳንድ ግለሰቦች ተስፋዬን ሲተቹ ከመጽሐፉ ሳይሆን ከኤርራዊነቱ ሲጀምሩ እመለከታለሁ ። ምንም እንኳ ወደ ኤርትራ ያደረገው ጉዞ ቢያስጠረጥረውም መጽሐፉን ለመተቸት ግን ዋነኛው መንስዔ መሆን የለበትም ።ብዙ ኤርትራውያን ኢትዮጵያዊነታቸውን ጠብቀው እስከ አሁን እንዳሉ ከቶ ሊዘነጋ አይገባዉም ።አቶ ተሰፋዬ ግን አትዮጵያን ለመጉዳት ኤርትራዊ ፣ ኤርትራን ለመጥቀም ኢትዮጵያዊ የሚሆኑ ከሆነ ወይም ከኦሮሞ ዝምድና ጉያ ተመስገዉ በኢትዮጵያዊነት ላይ ጦር ሲወረዉሩ ከተስተዋሉ የብዙዎቹ ተቃዋሚዎቻቸው አባባል ልክ ነው ማለት ነው ። ከዚሁ ጎን ለጎን የወያኔን ጉድ አጋለጥኩ የሚሉን አቶ ተስፋዬ ዛሬ ዛሬ ኤርትራ ውስጥ ያለውን ችግር ደብቀውት ሊኖሩ አይቻላቸዉም።

ተስፋዬ ገብረ አብ (እንዳቅሚቲም ብትሆን ) ስልጣን ላይ ከነበሩበት ወቅት ጀምሮ እስከ ዛሬ በደራሲያን ላይ ያለው ችግር ብዙ ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ደራሲያን በገንዘብ እጥረት 500 ወይም 1000 ብዛት ያለው እትም ነው ማሳተም የሚችሉት ። ነገር ግን በወያኔ አባላት ንግድ ዘርፍ ውስጥ የተሰባሰቡት የማተሚያ ድርጅቶች በድብቅ በብዙ ቁጥር መጽሐፉን ደግመው በማተም እየሸጡ ይጠቀማሉ ። የተሠሩት ቴያትሮች እየተኮረጁ በሲዲ እየተቀዱ በየቤታችን ተከምረው ይገኛሉ ። ሁላችንም ያልገዛነውን ፊልም ኮርጀን ስንመለከት ሌቦች መሆናችንን እንዘነጋለን ። በመንግሥት ስልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጦ ወንጀል ያልሠራ መጽሐፉ አይሸጥለትም ። ይህ የሃገራችንን ሥነ ጽሁፍ ሊገድል እንደሚችል ማወቅ አለብን ።

የመንግሥት ስልጣን ይዞ ሲበድለን የነበረ ሰው አሁን በእኛው ላይ የሠራውን በደል በመጻፍ እንደገና በእኛው ላይ እንዲያተርፍብን ልንፈቅድ አይገባም ። ገራፊው ስለገደለው ቢጽፍ ፣ ሟች ሰለተጎዳ ማልቀሳችንን ትተን፣ ገዳይን እንኳን ገደልክ ብለን፣ መጽሐፍቱን ገዝተን፣ ሀብታም ማድረግ ምን ያህል ሀሞተ ቢስ መሆናችንን ነው የሚያሳየው ። ለዚያውም እነዚህ ባለ ጊዜዎች ለገደሉን ፣ለጨቆኑን ፣ የደረሰብንን ግፍ የማናውቀው ይመስል ለመግዛት ስንሟሟት ለተመለከተ እብደታችንን ሳይረዳ አይቀርም ።

በሃገር ውስጥ ያሉ ደራሲያን መጽሐፋቸው በሕዝብ እንዲነበብ የግድ በሕዝብ ላይ ግፍ መሥራት የለባቸውም። በኑሮ ልምድ የሰበሰቡትን ታሪካቸውን ለማንበብ መቁረጥ አለብን ።መጽሐፍቶቻቸውን እየገዛን በገንዘብ ልንረዳቸው ያስፈልገናል። ቴያትሮችን ሰርቀን ማየት ትተን ዋናውን ቅጂ ብንገዛ ብዙ ደራሲያንን ልንደግፍ መቻላችንን ማወቅ ይኖርብናል ። የሰሞኑን የተስፋዬን መጽሐፍ ለመሸመት የተሯሯጡ ሁሉ ሌሎች ደራሲያን የጻፏቸውንም መጽሐፍት ለመግዛት እንቅልፍ ማጣት ይኖርባቸዋል ።

ዛሬ ከሀገራችን መጽሐፍቱን እየገዙ እያመጡ የሚሸጡት የወያኔ ሰዎች ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኙት ትርፍ የአንበሳ ድርሻ ሲሆን ደራሲያኑ ግን በልፋታቸው ሌሎች ሲበለፅጉበት ከማየትና እንባቸውን ወደ ሰማይ ከመርጨት በስተቀር የወያኔ አባላትን ተዋግተው ራሳቸውን ከመጉዳት በስተቀር የሚቀይሩት ጉዳይ የለም ። በየሀገሩ ያሉ የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲዎች መጽሐፍቱን ከደራስያኑ ተረክበዉ በማምጣት ለሕዝብ ሸጠው ገንዘቡን ለባለቤቶቹ ለማድረስ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

ይህን ጽሁፍ ልጨርስ ስል ለጽሁፌ መነሾ የሆነኝ የሜክሲኮአዊዉ ማሪዮ ቤላቲን የኪራይ ታሪክ ዳግም ታወሰኝ።የቅጥረኛ ጸሐፊዎቹን ጉዳይ ትተን ወደ ቅጥረኛ ፖለቲከኞቹ ስንገባ ሰሞኑን አዲስ አበባ ውስጥ ከተፈጠረው የአንድ ድርጅት ቡጢ ቀመስ ብጥብጥ በፊት አንዱ የወቅቱ ቡጢኛ አዛዉንት ለፓልቶክ ቀርበው የድርጅቱን ሀላፊዎች የወር ደሞዝ በሚመለከት የሰጡትን ቃለ መጠይቅ በሰማሁ ጊዜ ታላቅ ደስታ ተሰማኝ ። አዛዉንቱ የድርጅቱ መሪዎች በወር እስከ አራት ሽህ ብር ደሞዝ ያገኛሉ ነበር ያሉን ። የሚታገልልን ቀጠርን ማለት ነው። ካሁን ወዲህ ትግል ደህና ሰንብች አልኩኝ ።---ትቅር !--- አረ ጥርቅም ትበል ! ። ማሪዮ ቤላቲኒ እንዳለው ቀጥረን የምናታግል ከሆነ ታዲያ ምንድነው ችግሩ ? ድርጅት ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ፣ ሊቀመንበር ፣ ፀሐፊ ፣ አባል ብሎ መጨነቅ ቀረ ማለት ነው። የድርጅት መሪዎች ተከፍሏቸው ታግለው ግብ ሲደርሱ በሚፈጥሩት የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ አብረን እንዘንጣለን ። በትግሉ ውስጥ ለሚያስፈልጋቸው ብቻ ሳይሆን ለክብር መጠበቂያቸውም ጭምር ደሞዝ ያውም ጠቀም ያለ ደሞዝ ከተሰጠ ፣ ይህንን የሥራ ቦታ ለማግኘት መሪ የሚሆኑ ሰዎች ማመልከቻቸውን ይዘው እንዲቀርቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ለኢትዮጵያውያን በሙሉ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሊያወጡ ይገባል _ እኩልነት ለሁሉም እስከተባለ ድረስ ። ምን አልባት መሪዎቻችንን ማሟላት አለባቸው የሚባል መመዘኛ በቅርብ ቀን በድረ ገጾች የወጣውን አይነት መስፈርት ሊወጣ ይገባል ። ድብድቡ ለሥልጣኑና ለቦታው ከሆነ ደግሞ ጠንካራውንና ባንድ ቡጢ ጥርሶች የሚያስዉጣዉን ደንደሮ መርጠን ሊቀመንበር ማድረግ ነው ።ችግሩና መከፋፈሉም በዚሁ ይቆማል። ከሽተቱ አይቀር ጥንብት ነዉ ፡ መዝቀጥም እንደዚያዉ ።

ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም !

Beljig.ali@gmail.com